# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት

## ትእዛዝ

## (በ3/30/21 የተሻሻለው)

በማርች 18፣ 2020 በተላለፈውና በመይ 29፣ 2020 ዳግም በተረጋገጠው ትእዛዝ መሰረት፣ ጆይንት ኮሚቲ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) አሁን ባለው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜና ለፍትህ አስተዳደርም የተሻለ ስለሆነ፣ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ ትእዛዞች የማስተላለፍ ስልጣን ለዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ሰጥቷል።

በማርች 18፣ 2020፣ በማርች 19፣ 2020፣ በመይ 14፣ 2020፣ በጁን 19፣ 2020፣ በኦገስት 13፣ 2020፣ በኖቬምበር 5፣ 2020፣ እና ጃንዋሪ 13፣ 2021 በተላለፉት ትእዛዞች፣ ዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) እንደሚከተለው ብሎ ነበር፡ (በግልጽ ካልተጠቀሰ በስተቀር) ሁሉም ከጁን 19፣ 2020 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ የአሁኑ የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ (ጁዲሽያል ኢመርጀንሲ) በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆሙ (ቶል ይደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘሙ ዘንድ ታዟል። በትእዛዙ እንደተመለከተው፣ የጊዜ ገደቦቹ፣ ሁኔታዎች ሲቀየሩ ለተጨማሪ ጊዜ ሊታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ሊቆሙ (ቶል ሊደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ሊራዘሙ ይችላሉ። እገዳው፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሙ (ቶል መደረጉ)፣ እና መራዘሙ በዚህ ትእዛዝ በሰፈረው መሰረት ቢያንስ እስከ መይ 20፣ 2021 ድረስ ይቀጥላል። ፍርድ ቤቱ ሁሉንም እገዳዎች፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሞች (ቶል መደረጎች) እና የመራዘሚያ የጊዜ ገደቦች ከማብቃታቸው ቢያንስ ከ60 ቀናት በፊት ማስታወቂያ ያቀርባል።

ፍርድ ቤቱ እስከ መይ 20፣ 2021 ድረስ የሚሰማቸው የጉዳዮች አይነቶችና ብዛት በማስፋት ይገኛል።

የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጠበቆች፣ ተከራካሪ አካላት፣ እና የህብረተሰብ አባላት ደህንነትና ጤና ይጠበቅ ዘንድ፣ ከተወሰኑት የወንጀለኛ ክፍል እና የቤት ውስጥ ብጥብጥ ችሎቶች በስተቀር፣ ሁሉም የጉዳይ አይነቶች በርቀት (ሪሞትሊ) ይሰማሉ፣ በርቀት የማይሰሙትም በከፊል በርቀት የሚካሄዱ ይሆናሉ።

የጉዳዩ አይነት ከታች እስካልተዘረዘረ ድረስ፣ ሁሉም እስከ መይ 20፣ 2021 ድረስ ተቀጥረው የነበሩ ቅድሚያ-የማይሰጣቸው (ናን-ፕራዮሪቲ) ጉዳዮች ተለዋጭ ቀጠሮ

ይሰጣቸዋል፣ አዲስ ቀነ ቀጠሮ ይያዝላቸዋል፣ አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮች ተይዞላቸው ባለ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይቀጥላሉ፣ ከታች እንደተቀመጠውም ይሰማሉ። ጉዳዮቹን የሚሰሙ ዳኞች እንደየ አስፈላጊነቱ ስለሚሰሟቸው ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ ትእዛዞች ያስተላልፋሉ።

የኮቪድ-19 ምልክቶች ያለባቸው ጠበቃም ይሁን ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት መግባት የለባቸውም። https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/symptoms.html ይመልከቱ።

ማንኛውም ከነዚህ ለውጦች እፎይታ (ረሊፍ) መጠየቅ የሚፈልግ አካል በተገቢው የፍርድ ቤት ክፍል ማመልከቻ ፋይል በማድረግ እፎይታ ይሰጠው ዘንድ መጠየቅ ይችላል።

ፋይል ለሚደረጉ ማመልከቻዎች (ፕሊዲንግስ)፣ አቤቱታዎችና አዳዲስ ጉዳዮች ለመቀበል፣ ሁሉም ክፍሎችና (ዲቪዥንስ) የቤተሰብ ፍርድ ቤት በርቀት (ሪሞትሊ) ክፍት ይሆናሉ። በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረጉ ይቀጥላል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለርክ'ስ ኦፊስስ) የርቀት ክወናዎች (ሪሞት ኦፐሬሽንስ) ማስታወቂያዎችን ይመልከቱ። http://www.dccourts.gov/coronavirus

ፍርድ ቤቱ በዚህ ወቅት በተወሰኑ ሁኔታዎች ክፍያዎች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በመቀበል ይገኛል። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ https://www.dccourts.gov/services/online-payment ይመልከቱ።

በሕግ እስከ ተፈቀደ ድረስ፣ በርቀት የሚደረጉ ችሎቶች ለማህበረሰብ አባላት ቀጥተኛ ተደራሽነት ይኖራቸዋል። በርቀት በሚደረጉ የፍርድ ቤት ችሎቶች በቀጥታ እንዴት መስማት/መከታተል እንደሚቻል ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ተለጥፏል። https://www.dccourts.gov/services/remote-hearing-information

ፍርድ ቤቱ እንደየ ሁኔታዎቹ ተጨማሪ ማስተካከያዎች ያደርጋል። አብዛኛዎቹ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት ለሚከናወኑ ስራዎች (ሪሞት ኦፐሬሽንስ) ጥቅም ሊውሉ ይችላሉ፣ ፍርድ ቤቱ ለተቀሩት የፍርድ ቤት ክፍሎች በተቻለ መጠን በቅርቡ ተገቢውን መሳሪያ ይገጥማል። ተጨማሪ የፍርድ ቤት ክፍሎች ለችሎት ክፍት እየሆኑ ሲመጡ የያንዳንዱ ክፍል ጉዳዮች የሚዳኙ ዳኞች ቀነ ቀጠሮ የሚያዝላቸውና የሚሰሟቸው ጉዳዮች ሊያሳውቁ ይችላሉ።.

ፍርድ ቤቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች በዋናነት በርቀት (ፕራይመርሊ ሪሞትሊ) ይሰራል፡

## <u>የፍትሐብሄር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በህጎች (ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦችም (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ጭምር)፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ባለበት ጊዜ አይታገዱም፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው አይቆሙም (ቶል አይደረጉም)፣ እንዲሁም ደግሞ አይራዘሙም። እንዲህ የማይሆንባቸው የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡ (1) በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ህጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራቶርየም) የሚመለከታቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦች (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽን) ክልከላው እስኪያበቃ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም፣ እና (2) በሱፒርየር ፍርድ ቤት የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ የስነ ስርአት ደንቦች (ሩልስ ኦፍ ፕሮሲጀር) ደንቦች (ሩልስ) 16(a)(4) እና 16(c) መሰረት ከመኖሪያ ቤት ማስወጪያ ትእዛዝ (ሪትስ ኦፍ ረስቲቱሽን) ትክክለኛነት እና መሰጠት የተመለከቱ በአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎታቸው ያበቃ የነበረ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

የፍትሐብሄር ክፍል በሚከተለው መልኩ ይሰራል፡

- ዳኞችና የክፍሉ ሰራተኞች (ዲቪዥን ስታፍ) በርቀት መስራት ይቀጥላሉ። ዳኞች በምናባዊ (ቨርቹዋል) የፍርድ ቤት ክፍሎች ችሎቶች በሳምንት ለአምስት ቀናት ያህል በርቀት ያካሂዳሉ። በአካል እንዲቀርቡ በዳኛው ካልታዘዙ በስተቀር ማናቸውም ተከራካሪ አካላት ወይም ጠበቆች በአካል መቅረብ የለባቸውም።

- ማናቸውም የአስቸኳይ ማመልከቻ (ኢመርጀንሲ ሞሽን) ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

- የፍትሐብሄር ክፍሉ፣ ለአካላቱ ተገቢ ማስታወቂያ በመስጠት፣ በጁሪ-ለማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) በርቀት ሊያከናውን ይችላል። የፍትሐብሄር ክፍል ከመይ 2021 ጀምሮ በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ-ትራያልስ) ማካሄዱ ዳግም ለመቀጠል አቅዷል። የፍትሐብሄር ክፍል በፍርድ ቤት በአካል የሚሰሙ በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች (ጁሪ-ትራያልስ) ወይም በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) ቀጠሮ በሚይዝበት ጊዜ፣ የክርክሩ ቀጠሮ የሚሰጠው ሁሉም አካላት በተገኙበት ችሎት ወይም ማንኛውም በፍርድ ቤት በአካል ከሚደረጉ በጁሪ-ከማይዳኙ ክርክሮች (ናን-ጁሪ ትራያልስ) የቀጠሮ ቀን 30 ቀናት አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፣ በጁሪ-የሚዳኝ ክርክር (ጁሪ-ትራያል) ከሆነ ደግሞ 60 ቀናት

አስቀድሞ በጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ይሆናል፣ ይህ የሚሆነው ለጠበቆችና አካላት ምስክሮች በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሰፒና) ማቅረብ እንዲችሉና ለክርክሩ እንዲዘጋጁ በቂ ጊዜ ለመስጠት በማሰብ ነው።

- የፍትሐብሄር ክፍል፣ ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች (ኤቪደንሻሪ ሂሪንግስ) እና ዳኛ የሚዳኛቸው ክርክሮች (ቤንች ትራያልስ) ጨምሮ፣ በማንኛውም ተገቢ በሚሆንበት ሁኔታ ችሎቶች በርቀት ያከናውናል።

- ሁሉም ከኪራይ ቤት የማስወጣቶች (ኢቪክሽንስ)፣ የመኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር) የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) የፍርድ ቤት ሂደቶች፣ ህግ እስከሚፈቅደው ድረስ ተግባራዊ ሳይሆኑ ይቆያሉ።

- ምክኒያቱም (1) ፍርድ ቤቱ ከመኖሪያ ቤት የማስወጣት ውሳኔዎች (ጃጅመንትስ ፎር ፖሴሽን ኤንድ ሪትስ ኦፍ ረስቲቱሽን) በፍትሀዊና ስርአቱ በጠበቀ መልኩ እየተፈጸሙ እንደሆነ የማረጋገጥ ተፈጥሮአዊ ስልጣን ስላለው፣ (2) ፍትሀዊና ስርአቱ የጠበቀ ከመኖሪያ ቤት የማስወጣት ትእዛዝ (ሪት ኦፍ ረስቲቱሽን) አፈጻጸም በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ምክኒያት ለበርከት ያለ ጊዜ ከመኖሪያ ቤት ማስወጣቱ (ኢቪክሽን) የተላለፈ ሲሆን አከራዮች ከመኖሪያ ቤት የማስወጣቱ ቀጠሮ ሲሰጡ ምክኒያታዊ የሆነ ማስታወቂያ እንዲሰጡ የሚያስገድድ ስለሆነ፣ ነገር ግን በሙቀት ወይም በዝናብ ምክኒያት ለአጭር ጊዜ የተላለፈ ከሆነ ይህ ማድረግ አይጠበቅባቸውም፣ እና (3) በዲ.ሲ. ኮድ § 42-3505.01a በሚያዘው መሰረት የተለዋጩ ቀን ማስታወቂያ በመስጠት በኩል ምክኒያታዊ ያልሆነ ወይም ከባድ ጫና በአከራዮች ማሳረፍ ተገቢ ስላልሆነ፣ በማርች 16፣ 2020 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ ከመኖሪያ ቤት ለማስወጣት ቀጠሮ ተይዞለት የነበረ ህጉ እንዲቆይ የሚፈቅደው ጊዜ ካበቃ በኋላ ሌላ ከመኖሪያ ቤት የማስወጣት ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ፣ ማንኛውም አከራይ የዲ.ሲ. ኮድ § 42-3505.01a በሚያዘው መሰረት ከመኖሪያ ቤት ለማስወጣት ዳግም ቀጠሮ ከተያዘለት ቀን ቢያንስ ከ21 ቀናት አስቀድሞ ማስታወቂያ መላክ ይኖርበታል።

- የፍትሐብሄር ክፍል ተፈጻሚነታቸው ባልታገደ የኪራይ ቤት ማስወጣቶች (ኢቪክሽን)፣ መኖሪያ ቤት ሀራጅ (ፎርክሎዠር)፣ እና የእዳ ስብሰባ (ዴት ኮሌክሽን) ጉዳዮች የርቀት ችሎቶች ወይም በደረሱ ማመልከቻዎች ውሳኔ (ሩል ኦን ራይፐ ሞሽንስ) ሊያካሂድ ይችላል። እነዚህ ጉዳዮች በመይ 7፣ 2020 የእዳ ስብሰባ ጉዳዮች በተመለከተ የወጣው አጠቃላይ ትእዛዝ የማይመለከታቸው የአነስተኛ የይገባኛል ጉዳዮች (ስሞል ክለይምስ) ወይም የእዳ ስብሰባ ጉዳዮች እና የአከራይና ተከራይ ጉዳዮች ሕጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራተርዩም) የማይመለከታቸው፣ እንዲሁም ደግሞ ሌሎች እንደነ መጥሪያ ማድረስ (ሰርቪስ ኦፍ ፕሮሰስ)፣ የአንድ አካል ብቻ በመስማት መወሰን (ኤክስ ፓርተ ፕሩፍ)፣ እና የመከላከያ ትእዛዞች (ፕሮቴክቲቭ ኦርደርስ)

የመሳሰሉ ተገቢ ሊሆኑ የሚችሉ የማመልከቻ ችሎቶች ወይም አጫጭር ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች ያካትታሉ።

- ምንም እንኳን ፍርድ ቤቱ በመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) በሚያዘው መሰረት በአካል የሚደረጉ ክፍያዎች የመቀበል ውሱን ችሎታ ቢኖረውም፣ ተከራይ ***በጥሬ-ገንዘብ ያልሆነ*** ክፍያን ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም መክፈል ይችላል፡ (1) ክፍያዎን ወደ አከራይና ተከራይ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በፖስታ በመላክ፡ Landlord and Tenant Clerk's Office, 510 4th Street NW, Room 110, Washington, DC 20001፣ (2) ክፍያዎን በሞልትርየ ኮርትሀውስ (የፍርድ ቤት ህንጻ) በሚከተለው አድራሻ በሚገኘው ላቢ ባለው መጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በማስገባት፡ 500 Indiana Avenue, NW, Washington, DC 20001፣ የመዝገብ ቁጥሩ (ኬዝ ናምበር) በክፍያው መጻፍ አለበት፣ (3) ክፍያዎን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በፍርድ ቤቱ ፖርታል በኩል፣ ይህ የሚሆነው የወር ጠቅላላ ክፍያው ከ$1,000 የማይበልጥ ሲሆን ነው። እባክዎ ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መፈጸም እንደሚችሉ የወጣውን የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለክር'ስ ኦፊስስ) አሰራር ማስታወቂያን ይመልከቱ፡ [https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Superior-Court-Clerks-Offices-Remote-Operations.pdf](https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Superior-Court-Clerks-Offices-Remote-Operations.pdf). ***በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች*** ፍርድ ቤቱ በውሱን ሁኔታዎች ሊቀበል ይችላል። ቀናትንና ሰአታትን በተመለከተ እባክዎ የጸሀፊ ቢሮዎች (ክለክር'ስ ኦፊስስ) ማስታወቂያን ይመልከቱ (ከላይ ያለውን ሊንክ ይጫኑ)። ተከራይ የመከላከያ ትእዛዙን ማሻሻያ ካላገኘና ክፍያውን ወደ ፍርድ ቤት ሬጂስትሪ ወይም በአስቸኳይ ጊዜ በቀጥታ ለአከራይ ካልፈጸመ፣ እና አከራዩ በመቀጠል ማእቀቦች (ሳንክሽንስ) ይጣሉ ዘንድ ከጠየቀ፣ ፍርድ ቤቱ ከሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች በተጨማሪ የህብረተሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታ ጋር የተያያዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባል።

- አስተዳደራዊ ትእዛዝ 06-17 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 06-17) ምን ይበል ምን፣ የመጥሪያ ማድረሻ ቃለ መሀላዎች (አፊዳቪትስ ኦፍ ሰርቪስ) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- አስተዳደራዊ ትእዛዝ 15-03 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 15-03) ምን ይበል ምን፣ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ጥሰቶች ጉዳዮችና፣ እንደነ ወሳኝ ኩነት ሰነዶች የማሻሻል ማመልከቻዎች፣ የስም ለውጦች፣ የጾታ ምደባዎች (ጀንደር አሳይመንትስ)፣ የውጭ አገር የፍርድ ቤት መጥሪያ (ፎረይን ሰፒና)፣ የፍትሐብሄር የንብረት መውረስ (አሰት ፎርፈይቸር) አቤቱታዎች፣ የመረጃ ስም ማጥፋት (ሊበልስ ኦፍ ኢንፎርሜሽን)፣ እና ጓዳዊ ክሶች (ፍርየንድሊ ሱትስ) ጨምሮ ሁሉም በጃጅ-ኢን-ቻምበርስ የሚሰሙ ጉዳዮች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

- ደንብ 5 እና 5-111 የሰፈረው ምን ይሁን ምን፣ ታትመው ያሉ (ሲልድ) ጉዳዮችና በመዝገብ ቁጥራቸው SLD የሚል ያለባቸው (ለምሳሌ፡2020 CABSLD 000001)፣ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሰነዶች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ባልታተመ (አንሲልድ) ጉዳይ፣ የታተሙና (ሲልድ) ያልተቀነሰባቸው (አንሪዳክትድ) ሰነዶች ወደ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በወረቀት በፖስታ ወይም በመጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በኩል ማስረከቡ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

- በርቀት የሚደረጉትን ችሎቶች ለማቀላጠፍ የፍትሐብሄር ክፍል ሁሉንም አካላት ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢ-መይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለፍትሐብሄር ክፍል ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) እንዲሰጡ ያበረታታል። እባክዎ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ከታች ወዳሉት የኢ-መይል አድራሻዎች ኢ-መይል ያድርጉ፣ ወይም ከታች ወደ ተዘረዘሩት ቁጥሮች ይደውሉ።

| | | |
|---|---|---|
| የፍትሐብሄር እርምጃዎች ቅርንጫፍ | CivilDocket@dcsc.gov | (202) 879-1133 |
| የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ | LandlordandTenantDocket@dcsc.gov | (202) 879-4879 |
| የአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ቅርንጫፍ | SmallClaimsDocket@dcsc.gov | (202) 879-1120 |

## የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ ስራ ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉ። ይህ የሚከተሉትና ሌሎችን ያካትታል፡ በደንቦች (ሩልስ)5.1 እና D.C Code § 231322(a) እና (b) መሰረት የተቀመጡ የመጀመሪያ ችሎቶች የጊዜ ሰሌዳዎች (ታይምላይንስ ፎር ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ እንዲሁም ደግሞ የሚከተሉትን ጨምሮ የክስ መመስረቻ የጊዜ ገደቦች (ኢንዳይትመንት ዴድላይንስ) እና የክርክር የጊዜ ገደቦች፣ እና በD.C. Code §§ 23-102, 23-1322(h), 24-801, and 24-531.01 et. seq. መሰረት የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች።

ከዚህ ቀደም የተላለፉ የሚከተሉት ትእዛዞች ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ተራዝመዋል፡

- በማርች 16፣ 2020 የተላለፈው የህግ አስከባሪዎች ለተጨማሪ ግለሰቦች በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) እንዲፈቱ ፈቃድ የሚሰጥ ትእዛዝ።

- በማርች 27፣ 2020 የተላለፈው ህግ አስከባሪዎች ለተወሰኑ የቀላል ወንጀል የዳኛ እስር ትእዛዝ (ሚስደሚነር ቤንች ዋራንትስ) አይነቶች ቁጥጥር ስር ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በፍርድ ቤት መጥሪያ (ሳይቴሽን) የመፍታት ስልጣን የሚሰጥ ትእዛዝ።
- በማርች 27፣ 2020 የተላለፈው የሳምንት መጨረሻ የእስር ፍርዶች (ዊክኤንድ ጀይል ሰንተንስስ) ያገደ ትእዛዝ።
- በኤፕሪል 1፣ 2020 የተላለፈው፣ ወደ ጎን ስለ ተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) እና የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ) እና የፕሮቤሽን ዝርዝሮች (ፕሮቤሽናሪ ተርምስ) ጉዳዮች እየወደቁ ያሉ ጊዜያትን ሁኔታ በተመለከተ ለማብራራት የወጣው ትእዛዝ።
- የችሎቶች የጊዜ ሰሌዳ ስነ ስርአት ያቋቋመ የወንጀለኛ ክፍል ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)፣ በፍርድ ቤት 213-R የችሎቶች የጊዜ ሰሌዳ ፕሮቶኮሎች ያቋቋመ ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)፣ የጊዜ ሰሌዳና የክርክር ዝግጁነት ችሎቶች ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)፣ እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ከእስር ለመውጣት አስቸኳይ አቤቱታዎች ፋይል ማድረጊያ ስነ ስርአቶች ያቋቋመ ትእዛዝ (ስታንዲንግ ኦርደር)።

የወንጀለኛ ክፍል እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የወንጀለኛ ክፍል በርቀት ወይም በከፊል በርቀት መስራቱን ይቀጥላል፣ ችሎቶች ከሰንትራል ሰልብሎክ፣ ዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል)፣ ሰይንት ኤሊዛቤት ሆስፒታል፣ ዲፓርትመንት ኦፍ ዩዝ ሪሀብሊቴሽን ሰርቪስስ፣ ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ እና ማህበረሰቡ በቴሌፎን ወይም ቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ።
- በእስር-ያሉ የወንጀለኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ዲተይንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) እና ሌሎች ማስረጃ የማይሰማባቸው ችሎቶች (ናን-ኤቪደንሻሪ ሂሪንግስ) ተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የዩናይትድ ስቴትስ ጠበቃ ጽህፈት ቤት ወይም የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ከተስማሙ መቀጠል ይችላሉ፣ ስምምነቱም ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድ መከልከል የለበትም።
- ሀያ ሁለት የፍርድ ቤይ ክፍሎች በርቀት ወይም በከፊል በርቀት ስራቸውን ያካሂዳሉ፣ በዋናነትም የሚከተሉት ተግባራት በማከናወን ያተኩራሉ፡

  <u>በከፊል በርቀት የሚሰሩ የፍርድ ቤት ክፍሎች፡</u>

  - C-10 – የእምነት ክህደት ችሎቶች (አሬይንመንትስ)፣ መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ)፣ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ ታስሮ ተመልሶ መቅረብ (ቤንጅ ዋራንት ሪተርንስ)፣ ወንጀለኛን ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ማስተላለፍ (ኤክስትራዲሽን)።

  - 112-R – በከፊል በርቀት የሚካሄዱ በእስር-የሌሉ ተከላካዮች ማስረጃ-በማይሰማባቸው ችሎቶች ከዳኛው ጋር በፍርድ ቤት የሚቀርቡባቸው፣ ቅድመ-

ክርክር (ፕሪ-ትራያል)፣ የፕሮቤሽን ምክንያት አሳይ (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ)፣ እና በዳኛ የእስር ፈቃድ መሰረት ወደ ፍርድ ቤት በአካል መምጣት (ዎክ-ኢን ቤንች ዋራንትስ) ጨምሮ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ (ናን-ዲተይንድ ሂሪንግስ) ችሎቶች።

- 203-R፣ 211-R፣ 215-R፣ እና 310-R – በከፊል ከርቀት የሚካሄዱ፣ ተከላካዮች ተቀባይነት ባለው ምርመራና የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ከዳኛው ጋር በፍርድ ቤት የሚቀርቡባቸው በእስር-ያሉ የሲ.ኤፍ.1፣ ሲ.ኤፍ.2 እና ሲ.ኤፍ.3 የወንጀለኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ) እና የቀላል ወንጀል የእስር ችሎቶች (ሚስደሚነር ዲቴንሽን ሂሪንግስ)።

- 202-R እና 316-R – በከፊል ከርቀት የሚካሄዱ በእስር ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ (ናን-ጁሪ) ችሎቶች እና የአቤቱታ ችሎቶች። ተከላካዮች ተቀባይነት ባለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። አካላትና ምስክሮች፣ ፍርድ ቤቱ በርቀት እንዲቀርቡ ያዘዘ ወይም የፈቀደ ካልሆነ በስተቀር፣ ዳኛ ፊት በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። ጉዳዮች ቀነ ቀጠሮ የሚሰጣቸው፣ በእስር ቤት የቆዩበት ጊዜና የምስክሮች ብዛት ያካተተ በርካታ መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፣ በአንድ ቀን ከአንድ የሲ.ኤም.ዲ. (CMD) ወይም ዲ.ቪ.ዲ. (DVD) በጁሪ-የማይዳኝ ክርክር/አቤቱታዎች (ናን-ጁሪ ትራያልስ/ሞሽንስ) በላይ አይቀጠርም።

<u>በጁሪ-የሚዳኙ ክርክሮች የፍርድ ቤት ክፍሎች (ጁሪ-ትራያል ኮርትሩምስ)፡</u>

- 301-R፣ 302-R፣ ጁሮር ላውንጅ – ሁሉም አካላትና ጁሪ ሊሆኑ የሚችሉ በፍርድ ቤት ክፍል ዳኛ ፊት የሚቀርቡበት በከፊል በርቀት የሚካሄድ የጁሪ መረጣ (እንደየ አስፈላጊነቱ ለጁሪ መረጣ ከሌሎች ዲቪዥኖች መጋራት ይቻላል)።

- 201-R እና 203-R – ፍርድ ቤቱ በርቀት እንዲቀርቡ ያዘዘ ወይም የፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም አካላት፣ ጁሮሮችና ምስክሮች በፍርድ ቤት ክፍል ዳኛ ፊት የሚቀርቡበት በከፊል በርቀት የሚካሄድ ጁሪ-የሚዳኝ ክርክር።

- የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪ-ትራያል ሰርቪስስ) ተወካዮች፣ የፕሮቤሽን መኮንኖች እና ተጠቂዎች በአካል መቅረብ ይችላሉ፣ ወይም በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌኮንፈረንስ መቅረብ መቀጠል ይችላሉ።

<u>በርቀት የሚሰሩ የፍርድ ቤት ክፍሎች (ኮርትሩምስ)፡</u>

- 111-R – በአደንዛዥ እጽ ፍርድ ቤት (ድራግ ኮርት) (ሰኞ/እሮብ) እና በአእምሮ ጤና ፍርድ ቤት (ሜንታል ሄልዝ ኮርት) (ማክሰኞ/ሀሙስ)፣ አንዳንድ ችሎቶች ለአርብ ሊቀጠሩ ይችላሉ፣ በችሎቱ ለሚሳተፉ ተከላካዮች በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች።

- 116-R –በእስር የሌሉ የቀላል ወንጀል ጉዳዮች በርቀት የሚካሄዱ ጉዳዩ ያለበት የሚታይባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)።

- 210-R፣ 220-R እና 319-R – በርቀት የሚካሄዱ አስቸኳይ የቦንድ ምዘና ማመልከቻዎች ጨምሮ በእስር-ያሉ የወንጀለኛ መሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባቸው ጉዳዮች (ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ ማተርስ)።

- 213-R – ጠዋት (ኤ.ኤም.) በርቀት የሚካሄዱ የክስ ማጠናቀቂያዎች (ዲስፖዚሽንስ)፣ የመጀመሪያ ችሎቶች መተዎች (ወይቨርስ ኦፍ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ) ወዘተ ጨምሮ በእስር-ያሉ መሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባቸው (ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ) ጉዳዮች፣ ከሰአት (ፒ.ኤም.) ተከላካይ ሳይቀርብ የሚካሄዱ በእስር-ያሉ የመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንስ (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ ኮንፈረንስ)።

- 218-R እና 311-R – በርቀት የሚካሄዱ የመሰረታዊና ማስረጃ-የማይቀርብባብቸው ጉዳዮች (ሳብስታንቲቭ ናን-ኤቪደንሻሪ ማተርስ) በእስር ያሉ ከዲ.ዋይ.አር.ኤስ. እና ቢ.አ.ፒ. ጉዳዮች፣ እና ከጉዳዩ ዳኛ ፊት ያሉ በእስር-የሌሉ ጉዳዮች።

- 312-R እና 313-R – በርቀት የሚካሄዱ፣ የፍርድ ቤት መጥሪያ የእምነት ክህደት ችሎቶች (ሳይቴሽን አረይንመንትስ)፣ ወደ ጎን የተተዉ ክሶች (ዲፈርድ ፕሮሰኩሺንስ) ወይም የፍርድ ስምምነቶች (ሰንተንሲንግ አግሪመንትስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያዎች (ዲስፖዚሽንስ) እና ፍርዶች (ሰንተንሲንግስ) በተመለከተ የተደረጉ ስምምነቶች ወይም የስምምነቶቹ ማጠናቀቅያ ጨምሮ ዩ.ኤስ.ኤ. (312-R) እና ኦ.ኤ.ጂ. (313-R) ክርክር የሚደረግባቸው በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ችሎቶች (ናን-ዲተይንድ ሂሪንግስ)።

- 314-R እና 321-R –በርቀት የሚካሄዱ፣ በእስር-ያሉ የጊዜ ሰሌዳና የክርክር ዝግጁነት ችሎቶች (ስኬጁሊንግ ኤንድ ትራያል ሬዲነስ ሂሪንግስ)፣ ተከላካይ ላይገኝ ይችላል።

- 317-R – በርቀት ከሰይንት ኤሊዛቤት ሆስፒታል የሚካሄዱ የአእምሮ ጤና ሁኔታ ትእዝብት የሚደረግባቸው (ሜንታል ኦብዘርቬሽን) እና ስምምነት ያልተደረሰባቸው የብቃት (ኮንተስትድ ኮምፒተንሲ) ችሎቶች።

በከፊል በርቀት በፍርድ ቤት ቁጥር 112-R የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክር እና ፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ) ችሎቶች እና ሁሉም በርቀት በፍርድ ቤት ቁጥሮች ወደ ሌላ ቀን አይሸጋገሩም። ሁሉም ሌሎች ፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ) ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጥባቸዋል፣ ኤ.ቪ.አር. ፋይል ቢደረግ የብሮቤሽኑ ማብቂያ ያቆማል (ቶል ይደረጋል)።

ሁሉም በእስር-ያሉና በእስር-የሌሉ (ዲተይንድ ኤንድ ናን-ዲተይንድ) ባሁኑ ጊዜ በርቀት ወይም በከፊል በርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች የችሎቶች ቀጠሮ ያላቸው ጉዳዮች ባሁኑ ጊዜ ተወስኖላቸው ባለ እለትና ሰአት ይቀጥላሉ።

ሁሉም በእስር-ያሉ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ስታተስ ሂሪንግስ) በርቀት ወይም በከፊል በርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች ሳይሆን በሌላ የፍርድ ቤት ክፍሎች የተቀጠሩ ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠት የለባቸውም፣ በፍርድ ቤት ክፍል 314-R እና 321-R በርቀት ሂደት ለማድረግ ቀጠሮው ወደ የጊዜ ሰሌዳ ችሎቶች (ስኬጁል ሂሪንግስ) ይቀየራል፣ ተከላካይ ላይቀርብ ይችላል።

በኦክቶበር 26፣ 2020 የወንጀለኛ ክፍል ከኖቨምበር 30፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) ለመቀጠል ፍላጎት እንዳለው የሚያሳይ የ30-ቀን ማስታወቂያ አቅርቦ ነበር። ተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የመንግስት ጠበቃ ከተስማማ፣ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድም አልስማማም ማለት አይገባም፣ በጊዜ ሰሌዳ ችሎት (ስኬጁሊንግ ሂሪንግ) አዲስ የክርክር ቀናት ይመደባሉ።

በጃንዋሪ 15፣ 2021 የወንጀለኛ ክፍል አስቀድመው ለክርክር ተቀጥረው የነበሩ በእስር-ያሉ በጁሪ-የሚዳኙ የከባድ ወንጀል 2 (ፌለኒ 2) ጉዳዮች ክርክሮች (ዲተይንድ ጁሪ ትራያልስ) ዳግም ለመጀመር የ60 ቀናት አስቀድሞ ማስታወቂያ አቅርቦ ነበር። የወንጀለኛ ክፍል ከመይ 1፣ 2021 በፊት በተስፋፉ የጉዳዮች ምድብ በጁሪ-የሚዳኙ ጉዳዮች ዳግም መጀመራቸው የሚያስታውቅ የ60-ቀናት ማስታወቂያ ያስተላልፋል። የተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የመንግስት ጠበቃም ከተቀበለ፣ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድም አልቀበልም ማለት የለበትም፣ በክርክር ዝግጁነት ችሎት (ትራያል ሬዲነስ ሂሪንግ) አዲስ የክርክር ቀን (ትራያል ዴት) ይሰጣል።

ሁሉም እስከ መይ 20፣ 2021 ድረስ ተቀጥረው የነበሩ በእስር-የሌሉ የከባድ ወንጀል ጉዳዮችና በጁሪ የሚዳኙ ክርክሮች በስምንተኛው የወንጀለኛ ክፍል የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ

(ማስፈንጠሪያ (ሊንክ)) መሰረት ወደሚቀጥለው ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚሰማበት ቀን (ስታተስ ዴት) ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ሁሉም አካላት በርቀት መቅረብ የሚችሉ ከሆነ፣ ችሎቱ ቀደም ባለ ጊዜ እንዲደረግ አካላቱ ከተስማሙ፣ አካላቱ ችሎቱ ቀደም ብሎ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

ከኤፕሪል 1፣ 2021 ጀምሮ የተላለፈ የቅጣት ውሳኔ (ዲፈርድ ሰንተንሲንግ) እና የተላለፈ ክስ (ዲፈርድ ፕሮሰኪዩሽን) ምዘና ቀናት ጨምሮ ሁሉም በእስር-የሌሉ የአቅጣጫ መለወጥ (ዳይቨርሽን) ጉዳዮች መጀመሪያ በተቀጠረው የፍርድ ቤት ቀናት ይቀጥላሉ፣ የሚቀጥሉትም ጉዮቹን የያዘ አቃቤ ህግ የዩናይትድ ስቴትስ አቃቤ ህግ ቢሮ (ዩ.ኤስ.ኤ.ኦ.) ከሆነ በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 312-R ሲሆን፣ ጉዮቹን የያዘ አቃቤ ህግ ጠቅላይ አቃቤ ህግ (ኦ.ኤ.ጂ.) ከሆነ ደግሞ በ313-R ይሆናል።

ከመይ 10፣ 2021 ጀምሮ የወንጀለኛ ክፍል የፍርድ ቤት መጥሪያ የእምነት ክህደት (ሳይቴሽን አረይንመንትስ) ችሎቶች በመጀመሪያው ወይም ተለዋጭ ቀናት በፍርድ ቤት ክፍሎች 312-R (ዩ.ኤስ.ኤ.ኦ. ጉዳዮች) እና 313-R (ኦ.ኤ.ጂ. ጉዳዮች) መስማቱ ይቀጥላል፣ እነዚህ ችሎቶች ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ ይሆናሉ። በተወሰኑ ጉዳዮች የፍርድ ቤት ቀናትና የመግቢያ (ሎግ-ኢን ማድረጊያ) መረጃ በድረገጹ የወንጀለኛ ዲቪዥን ክፍል ይለጠፋል።

ከመይ 10፣ 2021 ጀምሮ የወንጀለኛ ክፍል በሁሉም የቀላል ወንጀል ጉዳዮች ጉዳዩ ያለበት ሁኔታ ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ) በመጀመሪያው ወይም ተለዋጭ ቀናት በፍርድ ቤት ክፍል 116-R መስማቱ ይቀጥላል፣ እነዚህ ችሎቶች ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ ይሆናል። በአንዳንድ ቀናት፣ የተቀጠሩት ጉዳዮች ብዛት ታሳቢ ያደረገ ጉዳዮቹን ለመስማት ሁለተኛ የርቀት የፍርድ ቤት ክፍል ሊከፈት ይችላል። በተወሰኑ ጉዳዮች የፍርድ ቤት ቀናትና የመግቢያ (ሎግ-ኢን ማድረጊያ) መረጃ በድረገጹ የወንጀለኛ ዲቪዥን ክፍል ይለጠፋል።

## <u>የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) (ዲ.ቪ.ዲ.) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5ፒ.ኤም. ድረስ ከሰኞች እስከ አርብ ይገኛሉ።

- አብዛኛዎቹ ዳኞችና የፍርድ ቤት ክፍሎች ሰራተኞች በርቀት መስራቱ ይቀጥላሉ። በከፊል በርቀት በሚደረግ የፍርድ ቤት ክፍል በአካል እንዲቀርቡ ካልታዘዙ በስተቀር አካላት በዲ.ሲ.ዲ. የርቀት የፍርድ ቤት ክፍሎች በሚደረጉ ችሎቶች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረቡ መቀጠል ይችላሉ።

- በዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች ያሉ አካላት በኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረጉ መቀጠል ይኖርባቸዋል። የፍትሐብሄር ፋይል የሚደረጉ ነገሮች በwww.probono.net/dccourts በኩል፣ ወይም ወደ DomesticViolenceManagement@dcsc.gov ኢ-መይል በመላክ ሊደረጉ ይችላሉ።

- በቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የሚካሄዱ የፍርድ ቤት ሂደቶች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ተከራካሪ አካላት ወደ ፍርድ ቤት ክፍሉ እንዴት በቀጥታ መግባት እንደሚችሉ መመርያዎች ያገኛሉ። አካላት-ያልሆኑ የዲ.ቪ. ክፍል የጸሀፊ ቢሮን በ (202) 879-0157 በመደወል ወይም ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢ-መይል በማድረግ ወደሚፈልጉት ፍርድ ቤት ክፍል መግቢያ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

- ሰባት የፍርድ ቤት ክፍሎች ስራቸው በርቀት ወይም በከፊል በርቀት ያካሂዳሉ እና፣ ፍርድ ቤቱ ያዘዘ ከሆነ ስራቸው በአካል ያካሂዳሉ። እባክዎን ከታች ያሉትን የፍርድ ቤት ክፍሎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ ከተመደቡ የችሎቶች አይነቶች ጋር ይመልከቱ፡

  ኤፕሪል 1 – መይ 7: o 113 – የሲ.ፒ.አ. ጉዳዮች o 114 – የሲ.ፒ.አ. ጉዳዮች o 117 – ዋነኛ የቲ.ፒ.አ. ችሎቶች o 118 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች (ዲ.አ.ሲ. ችሎቶች) o 119 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች o JM-9 – ተጠባባቂ የቲ.ፒ.አ. ችሎቶች እና የልጅ ቀለብ ጉዳዮች o 108 – ቲ.ፒ.አ.ዎች፣ ልዩ ልዩ የዲ.ቪ. ጉዳዮች

  ከመይ 10 ጀምሮ፡ o 113 – የሲ.ፒ.አ. ጉዳዮች o 114 – የሲ.ፒ.አ. ጉዳዮች o 117 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች o 118 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች

119 – የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳዮች (ዲ.ኡ.ሲ. ችሎቶች) በማክሰኞና ሀሙስ ቀናት፣ በሰኞ፣ እሮብ፣ እና አርብ ቀናት በሲንየር ዳኞች የሚካሄድ ተጠባባቂ የሲ.ፒ.ኦ. ክርክሮች
o 108 – ዋነኛ የቲ.ፒ.ኦ. የፍርድ ቤት ክፍሎች o JM-9 –
ተጠባባቂ የቲ.ፒ.ኦ. የፍርድ ቤት ክፍሎች እና የልጅ ቀለብ ጉዳዮች

<u>የወንጀለኛ ጉዳዮች – የቤት ውስጥ ብጥብጥ ቀላል ወንጀል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሚስደሚነር) (ዲ.ቪ.ኤም.) እና የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ክሪሚናል ኮንተምፕት) (ሲ.ሲ.ሲ.)</u>

- ባሁኑ ሰአት ያለው የዲ.ቪ.ዲ. አሰራሮች እስከ አርብ እለት መይ 7፣ 2021 ድረስ ይቀጥላሉ። በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት ወይም በከፊል-በርቀት ቀጠሮ ከተያዘላቸው ችሎቶች በስተቀር ሁሉም ከኤፕሪል 1፣ 2021 እና መይ 7፣ 2021 ተቀጥረው የነበሩ ከእስር የተፈቱ ተከላካዮች የዲ.ቪ.ኤም. እና ሲ.ሲ.ሲ. ችሎቶች በዲ.ቪ.ዲ. ዳኛ በሚያስተላልፈው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ከመይ 10፣ 2021 ጀምሮ ሁሉም ከእስር የተፈቱ ተከላካዮች ጉዳዮች <u>**ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጣቸውም**</u> እና ተመድቦላቸው ባለ ቀንና ሰአት <u>**በርቀት**</u> ይቀጥላሉ።

- <u>ለተቀጠሩት ችሎቶች መቅረብ፡</u> የዲ.ቪ. ክፍል የወንጀለኛ የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት፣ በከፊል በርቀት ወይም በአካል መስራቱ ይቀጥላሉ። በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ተከላካዮች ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ወይም ከማህበረሰቡ (ኮሚኒቲ) እየቀረቡ በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ ይካሄዳሉ። ጠበቃ፣ የቅድመ-ክርክር አገልግሎቶች ተወካዮች፣ እና የፕሮቤሽን ኦፊሰሮች በአካል፣ ወይም ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ። ምስክሮች በያንዳንዱ ጉዳይ በፍርድ ቤቱ እስከተፈቀደ ድረስ ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት መቅረብ ይችላሉ።

- <u>በእስር-ያሉ የጊዜ ሰሌዳ ችሎቶች (ዲተይንድ ስኬጁሊንግ ሂሪንግስ)፡</u> በC-10 በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. ፍርድ ቤት ክፍል የተቀጠሩ በርቀት የሚካሄድ በእስር-ያሉ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ስታተስ ሂሪንግስ) ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጣቸውም። በነዚህ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንሶች (ስኬጁሊንግ ኮንፈረንስስ) ተከላካይ መቅረብ አያስፈልግም። አካላት ማስረጃ-የሚሰማባቸው የችሎት (ሳብስታንቲቭ ሂሪንግስ) ቀን ወይም ተጨማሪ የጊዜ ሰሌዳ ችሎት ለመጠየቅ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

- <u>በእስር-ያሉ ማስረጃ-የሚሰማባቸው ችሎቶች (ዲተይንድ ሳብስታንቲቭ ሂሪንግስ)፡</u> ተከላካይ በዲ.ቪ.ኤም. ወይም ሲ.ሲ.ሲ. ጉዳይ ምክኒያት በእስር ቤት ያለ በእስር-ያሉ ችሎቶች (ዲተንሽን ሂሪንግስ) እና ሌሎች ማስረጃ-የማይሰማባቸው ችሎቶች

በማክሰኞና ሀሙስ በርቀት በሚደረገው የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ተከላካዮች ከዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) በቪድዮ ወይም በቴሌፎን ይቀርባሉ።

- <u>በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ)</u>፡ በኖቬምበር 2፣ 2020፣ ዲ.ቪ.ዲ. ከዲሰምበር 2፣ 2020 ጀምሮ በእስር-ያሉ በጁሪ-የማይዳኙ ክርክሮች (ዲተይንድ ናን-ጁሪ ትራያልስ) መስማት ለመቀጠል የ30-ቀን ማስታወቂያ አቅርቦ ነበር። በእስር ያሉ ጉዳዮች በተመለከተ አካላቱ እንዴት መቀጠል እንደሚፈልጉ የሚሰማበት በርቀት የሚደረግ የጊዜ ሰሌዳ ችሎት (ስኬጁሊንግ ሂሪንግ) ለማዘጋጀት የፍርድ ቤት ጽህፈት ቤት (ቻምበርስ) አካላቱን ያገኛል። የተከላካይ ጠበቃ ከጠየቀና የመንግስት ጠበቃም ከተቀበለ፣ ምክኒያታዊ ባልሆነ መንገድም አልቀበልም ማለት የለበትም፣ አዲስ የክርክር ቀን ሊሰጥ ይችላል። ጉዳዮች ቀነ ቀጠሮ የሚሰጣቸው፣ በእስር ቤት የቆዩበት ጊዜና የምስክሮች ብዛት ያካተተ በርካታ መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፣ በአንድ ቀን ከአንድ የሲ.ኤም.ዲ. (CMD) ወይም ዲ.ቪ.ዲ. (DVD) በጁሪ-የማይዳኝ ክርክር/አቤቱታዎች (ናን-ጁሪ ትራያልስ/ሞሽንስ) በላይ አይቀጠርም።

- <u>የእምነት ክህደት ቃሎች (አረይንመንትስ)</u>፡ የቤት ውስጥ ብጥብጥ የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በፍርድ ቤት ቁጥር C-10 መስማት ይቀጥላሉ። የሲ.ሲ.ሲ. የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ።

- <u>ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)፡</u>

    - ከኤፕሪል 1 እስከ መይ 7 ድረስ በከፊል በርቀት በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል እሮብ እለት የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች አይራዘሙም። ከመይ 10 ጀምሮ በከፊል በርቀት የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች በሰኞና እሮብ ቀናት ይቀጠራሉ። ተቀባይነት ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ተከላካዮች ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። ሁሉም ሌሎች አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።
    - ከኤፕሪል 1 እስከ መይ 7 ድረስ ሙሉ በሙሉ በርቀት በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ማክሰኞ እለት ጠዋት የተቀጠሩ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች አይራዘሙም። ከመይ 10 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በማናቸውም ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ባሉ ቀናት ሊቀጠሩ ይችላሉ። ተከላካዮች ጨምሮ ሁሉም አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።

- ○ በኤፕሪል 1 እና መይ 7 መካከል የተቀተሩ የፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ ችሎቶች ለወደፊቱ ቀን ይቀጥላሉ። ማንኛውም ከመይ 7 በኋላ የተቀጠረ የፕሮቤሽን ምክኒያት አሳይ ችሎቶች፣ ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር በተመደበለት ቀን በርቀት በሚካሄድ የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ኤ.ቪ.አር. ፋይል ቢደረግ የብሮቤሽኑ ማብቂያ ያቆማል (ቶል ይደረጋል)።

- <u>ከእስር ለተለቀቁ ተከላካዮች የሚደረጉ ችሎቶች (ሂርንግስ ፎር ረሊዝድ ደፈንዳንትስ)</u>፡ በእስር-የሌሉ የወንጀለኛ ጉዳዮች (ናን-ዲተይንድ ማተርስ) አካላቱ ከጠየቁ እስከ መይ 7፣ 2021 ድረስ በርቀት ችሎቶች በሚሰሙ የፍርድ ቤት ክፍሎች ቀነ ቀጠሮ ሊያዝላቸው ይችላል። ከመይ 10፣ 2021 ጀምሮ ሁሉም ከእስር የተፈቱ ተከላካዮች ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ ምክኒያት አሳይ ችሎቶች፣ የእምነት ክህደት ቃል የሚሰጥባቸው ችሎቶች (አረይንመንትስ)፣ እና የአቅጣጫ መለወጥ (ዳይቨርሽን) ችሎቶች **<u>አይራዘሙም</u>**፣ ይልቁንም ተመድቦላቸው ባለ ቀንና ሰአት በፍርድ ቤት ክፍል 117 እና በፍርድ ቤት ክፍል 118 **<u>በርቀት</u>** ይካሄዳሉ።

- ፍርድ ቤት ሲመጡ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ እንዲታሰሩ የሚፈቅድ ማዘዣ (ዋክ-ኢን ቤንጅ ዋራንት) ጉዳዮች፡ ከኤፕሪል 1 እስከ መይ 7 ድረስ፣ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች በእሮብ እለት በፍርድ ቤት ቁጥር 118 ወይም በማንኛቸውም ሌላ ቀናት በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 112 ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ። ከመይ 10 ጀምሮ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች በሰኞ ከሰአት በፍርድ ቤት ቁጥር 117፣ በእሮብ ከሰአት በፍርድ ቤት ቁጥር 118፣ በማንኛውም ሌላ ቀን ደግሞ በፍርድ ቤት ቁጥር 112 ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ።

<u>የፍትሐብሄር መከላከያ ትእዛዞዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ)</u>

- የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)፣ በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለማቀላጠፍ ሁሉንም አካላት ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለመስጠት ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክ'ስ ኦፊስ) በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ያገኙ ዘንድ ያበረታታል። እባክዎ፣ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ይህንን የቴሌፎን ቁጥር ይደውሉ።

- የጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዞች ጥያቄዎች በርቀት መሰማት ይቀጥላሉ።

- ዳኛው በምናብ በተደረገው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ በኩል ቲ.ፒ.ኦ.ውን ካላራዘመ በስተቀር፣ ሁሉም ጊዝያዊ የመከላከያ ትእዛዞች (ቲ.ፒ.ኦ.) የሚያበቁባቸው ቀናት ጉዳዩ ፋይል በተደረገበት ቀን መሰረት ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት መሆን ይኖርበታል።

- አካላቱ ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በሰው በኩል የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል።

- እንዲራዘም ማመልከቻ ካልቀረበ በስተቀር፣ ሁሉም ሲ.ፒ.ኦ.ዎች ትእዛዙ ተግባራዊነቱ በሚያከትምበት ቀን ወይም በጁን 19፣ 2020፣ ከሁለቱም የኋለኛው ቀን፣ ተግባራዊነታቸው ያከትማል። የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳዮች አገልግሎት ማክተሚያ ጊዜ በማርች 19፣ 2020 እና መይ 14፣ 2020 ከተላለፉ የኮቪድ-19 ትእዛዞች ከነበረው የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል አቀራረብ የተለዩ ናቸው፣ ነገር ግን በኦገስት 14፣ 2020፣ ኖቨምበር 5፣ 2020፣ ጃንዋሪ 18፣ 2021፣ እና ማርች 31፣ 2021 ከወጡ ትእዛዞች ተመሳሳይ መሆኑ ልብ ይበሉ።

- ክፍሉ ከኖቨምበር 9፣ 2020 ጀምሮ አስቀድሞ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው የነበረ በፍትሐብሄር መከላከያ ትእዛዝ ካላንደር ያሉትን ሁሉንም ጉዳዮች መስማት ጀምሯል። ሲ.ፒ.ኦ. እንደገና ተግባር ላይ እንዲውል ለመጠየቅ ከሚደረጉ አቤቱታዎች እና አንድ አካል ሳይገኝ የተወሰኑ ውሳኔዎች ወደ ጎን ለመተው (ሰት አሳይድ ዲፎልት) ከሚደረጉ አቤቱታዎች በስተቀር፣ ሁሉም በኤፕሪል 1 እና መይ 7፣ 2021 መካከል ተቀጥረው የነበሩ የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳዮች፣ በዲ.ቪ.ዲ. ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በማርች 31፣ 2021 በሰጠው የሲ.ፒ.ኦ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት በተቀመጠው ቀን ይካሄዳሉ። ከመይ 10፣ 2021 ጀምሮ ሁሉም የሲ.ፒ.ኦ፣ ኤ.አር.ፒ.ኦ. እና ተመሳሳይ ጉዳዮች ጉዳዩ ፋይል ከተደረገ በኋላ ከሁለት ሳምንታት ገደማ ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ አካላቱ ከጠየቁና ፍርድ ቤቱም ክፍት ቦታ ካለው፣ አካላት የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳያቸው ከተመደበው ቀን የቀረበ የችሎት ቀን እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ።

- <u>አንድ አካል ብቻ ባለበት የተወሰኑ የሲ.ፒ.ኦ. ጉዳዮች (ዲፎልት ሲ.ፒ.ኦ. ከዝስ) የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣዎች (ቤንች ዋራንትስ)</u>፡ ከኤፕሪል 1 እስከ  መይ 7 ባሉ ጊዜያት፣ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው መልስ ሰጪዎች (ሪስፖንደንትስ) በእሮብ እለት በፍርድ ቤት ቁጥር 118 ወይም በማንኛቸውም ሌላ ቀናት በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 112 ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ። ከመይ 10 ጀምሮ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው መልስ ሰጪዎች (ሪስፖንደንትስ) በሰኞ ከሰአት በፍርድ ቤት ቁጥር 117፣ በእሮብ ከሰአት በፍርድ ቤት ቁጥር 118፣ በማንኛውም ሌላ ቀን ደግሞ በፍርድ ቤት ቁጥር 112 ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ።

በሲ.ፒ.ኦ. ምክኒያት የተነሱ የልጅ ቀለብ (ቻይልድ ሳፖርት) ጉዳዮች

- የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) ወደ ክፍሉ የተመደቡ የልጅ ቀለብ ጉዳዮች በምናባዊ የፍርድ ቤት ክፍል (ቨርቹዋል ኮርትሩም) ይሰማል። አካላት ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።

ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትእዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ)

- የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና የመጨረሻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ ጥያቄዎች መደረግ ይችላሉ፣ ወደ DVD@dcsc.gov ኢሜይል በማድረግም ፋይል መደረግ ይችላሉ። ማመልከቻው ከዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽ ማግኘት ይቻላል። የተመደበው ዳኛ ጉዳዩን በርቀት የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማዋል።

- ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ በስተቀር ሁሉም *የኤክስ ፓርተ* (አንድ አካል ብቻ) ኢ.አር.ፒ.ኦ. የሚያከትሙባቸው ቀናት ጉዳዩን እያየ ባለው የዲ.ቪ.ዲ. ዳኛ በጃንዋሪ 18፣ 2021፣ ወይም ማርች 31፣ 2021 በሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ መሰረት ይራዘማሉ።

- እንዲራዘም የሚጠይቅ ማመልከቻ ፋይል ካልተደረገ በስተቀር ሁሉም በተግባር ላይ ያሉ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በትእዛዙ በሰፈረው ማከተሚያ ጊዜ ተግባራዊነታቸው ያበቃል።

- ክፍሉ ከኖቬምበር 9፣ 2020 ጀምሮ በከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትእዛዝ (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበረ ጉዳዮች መስማት ጀምሯል። ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች ክርክሮችና ከኢ.አር.ፒ.ኦ.-ተዛማጅነት ያለቸው አቤቱታዎች በዲ.ቪ.ዲ. ጉዳዩን እያየ ባለው ዳኛ በጃንዋሪ 18፣ 2021፣ ወይም ማርች 31፣ 2021 በሰጠው የሲ.ፒ.ኦ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. የጊዜ ሰሌዳ ትእዛዝ በተቀመጠው ቀን ይካሄዳሉ። አካላት ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።

## <u>የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)</u>

በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በስራ ላይ እስካለ ድረስ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም፣ <u>ይህ የማይሆነው በሚከተሉት ነው፡</u>

1. <u>የበደል እና ቸልተኝነት (አቢዩዝ ኤንድ ኒግለክት) ጉዳዮች፣ እና ተያያዥ ጉዳዮች፡</u>

በቸልተኝነት ጉዳዮች፣ የጉዲፈቻ ጉዳዮች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ (ተርሚኔሽን ኦፍ ፓረንታል ራይትስ) ጉዳዮች፣ እና የሞግዚትነት ጉዳዮች ያሉ የማመልከቻዎች ልምድና ግኝት (ሞሽንስ ፕራክቲስ ኤንድ ዲስካቨሪ)፣ በተመደበው ዳኛ ካልታዘዘ በስተቀር በሱፒርየር ፍርድ ቤት ተገቢ ደንቦች መመራቱ መቀጠል ይኖርባቸዋል። ጉዲፈቻዎችና የሴፍ ፋሚሊ ህግ (ኤ.ኤስ.ኤፍ.ኤ.) የጊዜ ገደቦች ተግባር ላይ መዋልን ይቀጥላሉ።

የጉዲፈቻ አቤቱታዎች በ [https://dcscgov.app.box.com/f/aeaf4eb2153743519a495d3f95d26c93](https://dcscgov.app.box.com/f/aeaf4eb2153743519a495d3f95d26c93) በሚገኘው የዲጂታል መጣያ ሳጥን (ዲጂታል ድሮፕ ባክስ) በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ሁሉም ሌሎች በጉዲፈቻ ጉዳዮች የሚደረጉ ልውውጦች በርቀት በኢ-ፋይሊንግ/ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በኩል ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

2. <u>የቤት ውስጥ ግንኙነት ጉዳዮች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ ኬዝስ)፡</u>

በተመደበው ዳኛ ካልታዘዙ በስተቀር፣ ጠበቆችና አካላት ማመልከቻዎችና ተቃውሞዎች ፋይል ማድረግን ጨምሮ የሚመለከታቸው የስርዓት ደንቦችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም በማርች 20፣ 2020 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ በተሰጡ ትእዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። ሁሉም ከማርች 20፣ 2020 በፊት በተሰጡ ትእዛዞች ያሉ የጊዜ ገደቦች በ90 ቀናት ተራዝመዋል።

ግለሰቦች ማህበራዊ ርቀትንና መጥሪያ ማድረስ (በአካልም ይሁን ሰርቲፋይድ ፖስታ ለማግኘት ወደ ፖስታ ቤት በመሄድ) "በቅንነት የሚደረግ ሙከራ (ዲሊጀንት ኤፈርትስ)" የማድረጋቸው እድል የመነመነ ስለሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ትእዛዝ እስኪያስተላልፍ ድረስ፣ በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በጽሁፍ መልእክት (ቴክስት መሰጅ) ወይም በኢመይል በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሰነዶችና መጥሪያ ማድረስ ይፈቀዳል። መጥሪያው የሚያደርስ አካል ለተመደበው ዳኛ በሚያረካ መንገድ ማድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የተፈጸመው የማድረስ ዘዴ "ትክክለኛውን ማስታወቂያ ለመስጠት በምክንያታዊነት የተሰላ" መሆኑ የሚያሳይ መሆንን ያካትታል። በአካል ማድረስ በህግ፣ በዲ.ሲ. ኮድ §§ 13-332 (አቅመ አዳም ያልደረሱትን በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ 13-333 (ብቁ

ላልሆኑ (ኢንኮፐተንት) ሰዎች በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ እና 46-206 (ድጋፍ (ሳፖርት) የተመለከቱ ጉዳዮች በአካል ማድረስ ያስገድዳል) ጭምር፣ የተደነገገ ከሆነ አካላት በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማድረስ አይችሉም።

በሲፒርየር ፍርድ ቤት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ደንብ 5(d)(5)(B) መሰረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ አካላት የፍርድ ቤት ወረቀት ማድረሻ ቃለ መሀላ (አፊዳፊት ኦፍ ሰርቪስ ፕሮሰስ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል እንዲያደርጉ ይፈቅዳል።

3. <u>የአእምሮ ተሀድሶ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን) ጉዳዮች፡</u>

በአስተዳደር ትእዛዝ ቁጥር 00-06 መሰረት የምላሽ ሰጪዎች ጠበቆች የአሁናዊ ሁኔታ ሪፖርቶች ፋይል ማድረጉን መቀጠል ይኖርባቸዋል፣ እስከሚቻል ድረስም የምላሽ ሰጪዎች መረጃ መሰረት ያደረገ በፈቃደኝነት የሚደረግ ቁርጠኝነት ፈቃድ ሪፖርት (ሪስፖንደንትስ ሪፖርትስ ኦን ኢንፎርምድ ኮንሰንት ፎር ቮሉንታሪ ኮሚትመንት) እና የተተኪ ውሳኔ ሰጪ ሪፖርቶች (ሳብስቲቱት ደሲሽን ሜከር ሪፖርትስ) ፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል። አካላት ልዩ ሪፖርት ወይም የተወሰነ ሰነድ ፋይል እንዲያደርጉ የሚያዝ ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል። አካላት ማንኛውንም ነባር ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል (a) ተሳታፊዎች ስብሰባ እንዲያደርጉ የሚያዝ ወይም (b) ወረርሽኙ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በሚቻል መጠን ዲፓርትመንት ኦፍ ዲስኤቢሊቲ ሰርቪስስ (የአካል ጉዳተኞች ክፍል) የተወሰኑ አገልግሎቶች ወይም ድጋፍ እንዲያቀርብ የሚያዝ ትእዛዝ ማክበር ይኖርባቸዋል።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት የችሎቶች አይነቶችን በርቀት በማካሄድ ይገኛል፡**

<u>የበደል እና ቸልተኝነት ጉዳዮች፣ ተያያዥ ጉዳዮች:</u>

- የቸልተኝነት የመጀመሪያ ችሎቶች (ነግለክት ኢኒሻል ሂሪንግስ)
- አስቸኳይ ችሎቶች (ኢመርጀንሲ ሂሪንግስ)
- የክስ ማጠናቀቂያ (ዲስፖዚሽን) ችሎቶች
- የስምምነት ችሎቶች (ስቲፑሌሽን ሂሪንግስ)
- *ቲ.ኤ. ኤል.* (*Ta. L.)* ችሎቶች፣ ጉዲፈቻዎች፣ የወላጅነት መብቶች ማቆሚያ ማመልከቻዎች፣ እና የሞግዚትነት ክርክሮች ጨምሮ ማናቸውም አይነት ክርክሮች።
- የቤተሰብ እንክብካቤ ፍርድ ቤት ችሎቶች
- የቋሚነት ችሎቶች (ፐርማነንሲ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ምዘና (ረቪው ኦፍ ዲስፖዚሽን) ችሎቶች፣ እና የቅድመ-ክርክር ችሎቶች ቀነ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል ￼ ሌሎች ችሎቶች።

<u>የቤት ውስጥ ግንኙነቶች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ)፡</u>

- እንደየ የፍርድ ቤት ክፍል መገኘቱና ሌሎች ፍርድ ቤቱ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያስባቸው ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት በስምምነትም ያለ-ስምምነትም የሚከናወኑ ፍቺዎች፣ መለያየቶች፣ ባለአደራነት፣ የልጅ ቀለብ።
- የቤት ውስጥ ግንኙነት በዛኑ ቀን የሚካሄዱ አስቸኳይ ችሎቶች (ሴም ደይ ኢመርጀንሲ ሂሪንግስ)።
- ባለአደራነት ለማሻሻል የተደረጉትን ወይም በዛኑ ቀን እንዲደረጉ አስቸኳይ ችሎት ተጠይቆ የተከለከለበት የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ኮንተምፕት) አስቸኳይ አቤቱታዎች፣ ነገር ግን አቤቱታውን ባፋጣኝ መስማቱ አስፈላጊና የሚቻል መሆኑ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ከሆነ።
- እንደነ የግኝት አለመስማማቶች መፍታት ወይም ሌሎች ጉዳዮች፣ በርቀት መፈታት የሚችሉም፣ ወይም ለፍትህ ጥቅም አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው፣ የመሳሰሉ በዳኛ አስተያየት የሚፈቱ ጉዳዮች (ዲስክረሺናሪ ማተርስ)።

<u>የወጣት ጥፋተኛ ሀላፊነት አለመወጣት (ጁቬናይል ደሊኩዌንሲ)፣ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሰዎች፣ እና የግል ጉዲፈቻዎች፡</u> በፍርድ ቤቱ ካልታዘዘ በስተቀር፣ በአስቸኳይ ጊዜ መፈጸም የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ ሁሉም የጊዜ ገደቦች የአስቸኳይ ጊዜ በተግባር ላይ እስካለ ድረስ፣ ተጨማሪ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ፣ ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም። ይህ ትዕዛዝ ቢኖርም፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ያከናውናል፡

- ምክኒያታዊ ጥርጣሬ ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ) ጨምሮ የወጣት ጥፋተኛ የመጀመሪያ ችሎቶች (ጁቬናይል ኢኒሻል ሂሪንግስ)።

- ዳኛው ችሎቱን ማካሄድ ጉዳዩን ለመፍታት ጠቃሚ ነው፣ ወይም የጥፋተኛ ወጣቱ የእስር ጊዜ ሊቀይር ይችላል፣ ብሎ በማመን ከወሰነ፣ ማናቸውም ሌሎች ችሎቶች (ለምሳሌ፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የክስ ማጠናቀቂያ ችሎቶች (ዲስፖዚሽን ሂሪንግስ)) ሊደረጉ ይችላሉ፣ ይህ የሚመለከተው ለሆፕ (HOPE) እና ወጣት ጥፋተኛ የጠባይ አቅጣጫ መለወጥ (ጁቬናይል ቢሀቭዮራል ዳይቨርሽን) ፕሮግራም (ጀይ.ፒ.ዲ.ፒ.) የፍርድ ቤት ክፍሎች ነው።

- በወጣት ጥፋተኞች ጉዳዮች እውነታ ለማወቅ የሚደረጉ ችሎቶች፣ በርቀት ብቻ እና ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ እውነታ ለማወቅ የሚደረገውን ችሎት ለፍትህ ጥቅም ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስ ተጨማሪ ሊራዘም አይችልም የሚያስብል የተወሰኑ ምክኒያቶች የደረሰበት ከሆነ ብቻ፣ እና ከጠበቃ ጋር ከተመካከረ በኋላ በምላሽ ሰጪው ፈቃድ ብቻ የሚካሄዱ ናቸው። ማንኛውም አካል ምስክር ሊገኝ አይችልም ወይም

በሱፒርየር ፍርድ ቤት የወጣት ጥፋተኛ ደንቦች (ጁቭናይል ሩልስ) መሰረት በማንኛውም ሌላ ምክኒያት እውነታ ለማወቅ የሚደረገውን ችሎት እንዲራዘም መጠየቅ ይችላል። ሲፒርየር ፍርድ ቤት በጁራ-የሚዳኙ የወንጀለኛና የፍትሐብሄር ጉዳዮች ክርክሮች በአካል በፍርድ ቤቱ ማድረግ ሲጀምር የቤእተሰብ ፍርድ ቤትም ሁሉንም ደህንነት ለመጠበቅ የቀረቡትን ምክረሀሳቦች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የወጣቶች ቀላል ወንጀል (ዴሊኩዌንሲ) ክርክሮች በአካል ማካሄድ ይጀምራል።

- ልዩ ስደተኛ ወጣት ጥፋተኛ (ስፔሻል ኢሚግራንት ጁቭናይል) ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)።

- የግል ጉዲፈቻዎች (ፕራይቬት አዳፕሽንስ)።

<u>የአእምሮ ጤና (ሜንታል ሄልዝ)</u>፡

- የአእምሮ ጤና ምክኒያታዊ ጥርጣሬ ችሎቶች (ፕሮባብል ከውዝ ሂሪንግስ)።
- የአእምሮ ጤና ኮሚሽን ችሎቶች።
- የስረዛ ችሎቶች (ሪቮኬሽን ሂሪንግስ)፣ በሚያስፈልጉበት ጊዜ ጉዳዩ ያለበት የሚታወቅባቸው ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ አስቸኳይ ችሎቶች፣ ቅድመ-ክርክር ችሎቶች፣ እና ክርክሮች (ትራያልስ)።

<u>የአእምሮ ማጎልመሻ (ሜንታል ሀቢሊቴሽን)፡</u>

- የአእምሮ ማጎልመሻ ምዘና፣ እና አስቸኳይ ችሎቶች።

<u>የስም ለውጦች</u>፡

- የስም ለውጥ ችሎቶች ይካሄዳሉ።

<u>የወላጅነትና የድጋፍ (ፓረንቴጅ ኤንድ ሳፖርት) ጉዳዮች</u>፡

- ሁሉም ቀነ ቀጠሮ እየተሰጣቸው ነው፣ የሚቻል ከሆነም በወረቀት ያሉትን በመፍታት ይገኛል።

<u>ጋብቻዎች፡</u>

- የጋብቻ ስነ-ስርአቶች መፈጸም ዳግም ተጀምሯል፣ እና በዌብኤክስ በኩል እየተፈጸሙ ነው። የጋብቻ ምስክር ወረቀት የምትፈልጉ አካላት እባካችሁ የሚከተለውን ጎብኙ፡

https://www.dccourts.gov/form/marriage-application

ሌላ ተዛማጅነት ያለው መረጃ:

- የቤት ውስጥ ግንኙነቶች አስቸኳይ አቤቱታዎች ፋይል ማድረጊያ ሂደት:
    - በጠበቃ የተወከሉ አካላት ማናቸውም አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል።
        - አካላት "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - 501(c)(3) በሆኑ ድርጅቶች የተወከሉ ተከራካሪዎች እና ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪዎች አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይችላሉ።
        - አካላት "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ የተባሉ እና ኢፋይል ማድረግ ያልፈለጉ ተከራካሪዎች አቤቱታውን ወደ ኢመይል FamilyCourtCIC@DCSC.GOV አያይዘው መላክ ይችላሉ። ፋይል አድራጊዎች በእንደዚህ ኢመይሎች ሳብጀክት መስመር (Subject Line) "አስቸኳይ አቤቱታ (Emergency Motion)" ብለው መጻፍ ይኖርባቸዋል። ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ ለመባል ለመጀመሪያ ጊዜ እየጠየቁ ያሉ ተከራካሪዎች ጥያቄያቸውና አስቸኳይ አቤቱታውን ወደ FamilyCourtCIC@DCSC.GOV መላክና፣ በሳብጀክት መስመር (Subject Line) "አስቸኳይ አቤቱታና ከክፍያ ነጻ እባል ዘንድ እጠይቃለሁ (Emergency Motion and Fee Waiver Request)" ብለው መጻፍ ይኖርባቸዋል።
        - ራሳቸውን የወከሉና ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በመጠቀም ኢፋይል እያደረጉ ያሉ ተከራካሪዎች "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
    - ራሳቸውን የወከሉ፣ ከፋይል ማድረግያ ክፍያ ነጻ ያልተባሉ ተከራካሪዎች አስቸኳይ አቤቱታዎችን በ https://www.dccourts.gov/superior-court/efiling በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በመጠቀም ኢፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል።

- አካላት "አስተያየቶች (comments)" በሚል ክፍል አስቸኳይ ችሎት (ኢመርጀንሲ ሂሪንግ) እየጠየቁ እንዳለ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

○ ፋይል አድራጊ አቤቱታውን ከላይ እንደተጠቀሰው አስቸኳይ መሆኑ በስነ ስርአት ካልለየ አቤቱታው በጊዜ ሂደት ላይደረግለት ይችላል።

- በቤተሰብ ፍርድ ቤት አዲስ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ፋይል የሚደረግበት ሂደት በፍርድ ቤቱ ድረገጽ በዝርዝር ይገኛል፣ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf ይመልከቱ።

- በቤተሰብ ፍርድ ቤት አዲስ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች አቤቱታዎች ወይም ማመልከቻዎች ፋይል የማድረግ ሂደት በዝርዝር በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ይገኛል፣ በ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf ይመልከቱት።

- የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) (202-879-0096) በቤተሰብ ፍርድ ቤት ጉዳዮች (ፍቺ፣ የልጅ ባለአደራነት (ቻይልድ ካስተዲ)፣ የልጅ ቀለብ፣ ወዘተ) መረጃ ለመስጠትና አካላት ሰነዶች ፋይል ማድረግ እንዲችሉ ለመርዳት በርቀት ይሰራል።

- ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤት መጥሪያዎች በኢሌክትሮኒካዊ መንገድ ይሰጣል፣ ፋይል ወዳደረገ አካልም በኢመይል ይልካል።

- የቤት ውስጥ ግንኙነቶች የመጀመሪያ ችሎት ቀን (ኢኒሻል ሂሪንግ) ፋይል በሚደረግበት ጊዜ ቀነ ቀጠሮ አይሰጥም፣ ምላሽ ሰጪ ሰነድ ፋይል ካደረገ ወይም ሰነዶች እንደደረሱ የቃለ መሀላ ማረጋገጫ (አፊዳቪት ኦፍ ሰርቪስ) ፋይል ከተደረገ በኋላ፣ እና የፍርድ ቤቱ አሰራሮች ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊደረግ የሚቻል ከሆነ ነው ቀጠሮ የሚሰጠው።

- ክትትል የሚደረግበት የጉብኝት ማእከል (ሱፐርቫይዝድ ቪዚቴሽን ሰንተር) የመግቢያ ቃለ ምልልሶችና (ኢንቴክ ኢንተርቪውስ) ክትትል የሚደረግባቸው ጉብኝቶች በርቀት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

- ባለ ብዙ-በር (መልቲ-ዶር) ሽምግልና እና የሽምግልና ምዝገባ በቪድዮኮንፈረንስ ወይም በቴሌፎን መሳተፍ ለሚችሉ አካላት በርቀት መደረግ ይችላል።

<u>የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች</u>

በግብር (ታክስ)፣ እና በኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የነበረ እግድ አሁን ተነስቷል፣ እና በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ባሁኑ ሰአት በሙሉ ሀይል ተግባር ላይ ይውላሉ።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

 ዳኞች የሚከተሉትን ጉዳዮች በርቀት በዌብኤክስ ይሰማሉ፡

- ○ የ21-ቀን አስቸኳይ ሞግዚቶች (ኢመርጀንሲ ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ
- ○ የ90-ቀን የጤና-ጥበቃ ሞግዚቶች (ሄልዝ-ኬር ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ
- ○ የአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ማመልከቻዎች (ፐቲሽንስ ፎር ጀነራል ፕሮሲዲንግስ) (የሞግዚትነት እና ተንከባካቢነት ማመልከቻዎች (ጋርድያን ኤንድ ኮንዘርቫቶርሺፕ ፐቲሽንስ)) – በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በፖስታ (ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ
- ○ ዳኛው ዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው ሌሎች የጣልቃገብነት ጉዳዮች (ኢንተርቬንሽን ማተርስ)
- ○ ዳኛው በዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው የንብረት ጉዳዮች (ኢስቴት ኬዝስ) ጨምሮ፣ ሌሎች የኑዛዜ ማረጋገጫ ጉዳዮች

- በርቀት ለሚካሄዱ ችሎቶችና የአዳዲስ ጉዳዮች ፋይል ማድረጎች ለማቀላጠፍ የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል ሁሉንም አካላት ፋይል ስለ ተደረጉ ጉዳዮች በተመለከተ፣ እንደነ አካላት ሊገኙባቸው የሚችሉ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ፣ የመገኛ መረጃዎች እንዲያቀርቡ ያበረታታል።
- የሞግዚትነት ቀጠሮዎች ሶስት ዓመታዊ ግምገማዎች ታግደዋል።

የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ዳኞችና ሰራተኞች (ስታፍ) በርቀት መስራቱ ይቀጥላሉ

- ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) እና ጉዳዩ ያለበት ሁኔታ (ስታተስ ሂሪንግ) ችሎቶች በዌብኤክስ በኩል በርቀት ይካሄዳሉ

የመጀመሪያ የጊዜ ሰሌዳ (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ)፣ የቅድመ-ክርክር (ፕሪ-ትራያል) ኮንፈረንሶች፣ እና ክርክሮች (ትራያልስ) በዌብኤክስ በኩል በርቀት ይካሄዳሉ

**<u>የኦዲተር ማስተር ቢሮ</u>**

ኦዲተር ማስተሩ ሁሉንም ችሎቶች በርቀት በዌብኤክስ በኩል እያካሄደ ነው። አካላት በቴሌፎን ወይም በቪድዮ-ኮንፈረንስ መሳተፍ ይችላሉ። በርቀት እንዴት መሳተፍ እንዳለብዎ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም አካላት ይሰጣሉ።

ኦዲተር ማስተሩ ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ ያስተላለፋቸውን ሁሉም ትእዛዞች አካላት ማክበር ይኖርባቸዋል። ቢሮው ባሁኑ ሰአት አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ የሁሉንም ችሎቶች ሌላ ቀነ ቀጠሮ የሚሰጥ ትእዛዝ፣ በአዳዲስ ጉዳዮች የችሎቶች ቀነ ቀጠሮ፣ እና ሰነዶች የሚቀርቡባቸው አዳዲስ ቀናት የያዙ የተለያዩ ትእዛዞችን በመስጠት ይገኛል።

ሰራተኞች (ስታፍ) በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ከሰኞ እስከ አርብ ይገኛሉ። ሰራተኞች ሁሉንም ሰነዶች በርቀት ሂደት እያደረጉ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ሰነዶች በኢመይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። በሚስጢር መያዝ የሚኖርባቸው (ሰንሲቲቭ ኢን ኔቸር) ሰነዶች በኢመይል በኩል ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov መላክ ይቻላል።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው ጉዳዮች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለአካላት እንዲደርሱ ይደረጋሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢመይል በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።